# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)


ጥቅምት ፮ ቀን ፪ ሽህ ዓ/ም

## አገራዊ ትግል አገራዊ ትኩረትንና ሕዝባዊ አክብሮትን ይጠይቃል!
## ወዴት እያመራን ነው?
## <u>ውይይት በአገር ጉዳይ፥ በቁም ነገር!!</u>

ውድ አገራችን በምትገኝበት እጅግ አስጊና አሳሳቢ ዓለም-አቀፍ ይዘት ባለው አካባቢያዊና የውስጥ ውጥረት የበዛበት ሁኔታ ላይ በተለይ ከሁለት ዓመታት ጀምሮ ከሳምንት ሳምንትና ከወር ወር እየተባባሰና እየተንሰራፋ የመጣው የለየለት አምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓት ታክሎበት፥ አገዛዙን ተቃውሞ ለለውጥ በሚታገለው ጎራ መኻል የታየው ቅጥ ያጣ በመርኅ ላይ የተመሠረተ አንድነት እጦት እና አሁን ደግሞ በተለይ በቅንጅት ወገኖቻችን በኩል የምንታዘበው ክስተት ሲጨመርበት ጥራት ስንል ውኸንብርን፥ የትግል አንድነት ስንል ክፍፍልን እያገዘ ሕዝባችን የታገለላቸውና የተሰዋላቸው የግንቦት ታሪካዊ እሴቶች ሰብሳቢ አጥተው ኢትዮጵያ ሁነኛ ባለቤት ያጣች አገር የምትሆንበት በፀፀት የማይመለስ አንገት አስደፊ አደጋ በዓይናችን ሥር እያቆጠቆጠ መሆኑን በአርምሞና በሃዘኔታ እያየን ነው።

ለመድብለ-ፓርቲ ኅብረተሰብ እየታገልን በማንኛውም ድርጅት ውስጥም ሆነ በድርጅቶች መኻል ልዩነቶች አይኑሩ አንልም። ይኖራሉ። መኖርም አለባቸው። ጥያቄው ያለውና እኛን በጣም የሚያሳስበን ግን ልዩነቶች በተከሰቱባቸው ድርጅቶች መኻል አሉ የተባሉ ልዩነቶች አያያዝ ላይና በዚሁ አለመግባባት ምክንያት በደጋፊዎች ዘንድ ጉዳዩን በተገቢ አብሰልስሎ በጥሞና ካልመረዳት በመነጨ የሚታየው ደፈናዊ አጋ በመለየት መፏከቱ በትግሉ ላይ ሊያስከትል የሚችለው እክል ነው።

ትግሉ መከራ ለበዛበት ሕዝባችንና ጎልውንዋ ከባድ ፈተና ውስጥ ለወደቀ አገር ነውና፥ ዛሬ በቅንጅት ውስጥ የተፈጠውን ችግር ለጠቅላላው ለትግላችን እንዳይተርፍ፥ ዛሬ ካለው ውኸንብር ትግላችንና መስመራችን ጥራት ይዞ እንዲወጣ ከተፈለገ የአገራችን ዴሞክራቶችና አገር-ወዳዶች የድርጅትንም ሆነ የግለሰብ ተገኸነትን አጥር ሰባብረው "ወዴት እየሄድን ነው? ወዴት እየወሰዳችሁን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች አቅርበው በቁም ነገር ላይ ያተኮሩ ጤናማ ክርክሮች እንዲካሄዱ መጠየቅ ይኖርባቸዋል። ወርቃማ ጊዜያችንን እጅ እግር የሌላቸው በሚመስሉ ንትርኮች ስናባክን ከምር ልብ አላልናቸው እንደሆን እንጅ ዛሬ በአገራችን ውስብስብ ሁኔታ ትግላችንን፥ ስትራቴጂያችንን በተመለከተ ብዙ ውይይትና ጥራት የሚፈልጉ ቁም ነገሮች አሉ።
እነዚህ ነጥቦች ምንድን ናቸው? ከነሱ አንፃር የኅብረታችን አቋም ምንድን ነው? ከዚህ አካሄድ ውጭ የሚቀርቡት ስትራቴጂዎች ምንድን ናቸው? አደጋቸውስ?

አንደኛ የእኛም ሆነ የሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች ዓላማ ምንድን ነው? ደጋግመን እንዳልነው ዓላማችን ኢትዮጵያን እርቅ ወደ ወረደበት፥ ዴሞክራሲና ፍትኅ ወደ ሰፈኑበት የተረጋጋ ኅብረተሰብ የማሸጋገር ዓላማ ነው።
በኛ እምነት ይኸ ታሪካዊ ተጋድሎ አንድ ወሳኝ ምእራፍ የሚደርሰውና እውን የሚሆነው በአገራችን ምድር በሚሰየም በአንድ ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባዔ አማካይነት ስለሆነ ሁላችንም ይኸን መፈክር አንግበን መታገል ይጠበቅብናል።

እንዲህ ዓይነቱ አገር-አቀፍ ጉባዔ በአጠቃላይ በአገራችን አሉ የሚባሉ የፖለቲካ ኃይሎች የሲቪኩ ማኅበራትና የነፃው ፕሬስ ተወካዮች፥ ከየአካባቢው የሚመጡ የአገር ሽማግሌዎች፥ የሐይማኖት አባቶች፥ የወጣቶች፥ የሴቶች፥ የሙያና ሌሎች ማኅበራትና ስብስቦች፥ ምሁራን፥ ወዘተ.. የሚሳተፉበትና የአገራችንን


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217;(Fax) 202-291-7645

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

እጣ ፈንታ ተወያይተው የሚቀይሱበት ጉባዔ ይሆናል፡፡ በአማራጭ ፕሮግራማችንም በግልፅ እንደተቀመጠው አገራችንን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እናሸጋግር ካልን የዚህ ኃላፊነት በዚህ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ ለሚመረጥ "የዴሞክራሲ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽ)ን ኮሚሽን" የሚተው ይሆናል፡፡ በአገራችን ትርጉም ያለው ብሔራዊ እርቅ ከተባለ የዚህ ኃላፊነት ደግሞ እንደዚሁ በዚህ ጉባዔ ለሚሰየም "የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን" መተው ይኖርበታል፡፡

ሁለተኛ ይኸን ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ጉባዔ በቅድሚያ በትግልና በሕዝብ ድል በተረጋገጠ ዴሞክራሲ ተጠቅሞ በሰከነ ውይይት የነገይቱን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በጋራ ስምምነት መልክ የሚያስይዝ ጉባዔ እንጂ በአገሪቱ የሌለ ዴሞክራሲን "የሚያመጣ" መድረክ አድርገን አናየውም፡፡ ከዚህ የምንደርስበት መደምደሚያ ግልፅ ነው፡፡ ዛሬ አገራችን  የምትገኝበት ሁኔታ እንኳን እንዲህ ዓይነቱ ሰፊ ውይይት ቀርቶ በቅድመ-ግንቦቱ ወቅት የነበሩት የዴሞክራሲ ፍንጮች ደብዛቸው የጠፋበት፥ በነፃ የመደራጀት መብት የተነፈገበት፥ በሕዝባችን የትግል ተሳትፎ ሕገ-ወጥ ተአቅቦ የተደረገበት፥ ነፃው ፕሬስ የወደመበት ሁኔታ ነው፡፡ እነዚህ መብቶችና ተቋማት ለዚህ ውድመት የበቁት በአጋጣሚ አይደለም፡፡ ከእንግዲህ የአሕዴግ መሪዎች በሥልጣን የመቆየታቸው ዕድል ተንጠልጥሎ የተያዘው እነዚህ ሴቶች ተመልሰው እውን አለመሆናቸውን በማረጋገጥ ላይ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ያለ መራራ ትግል ተመልሰው እውን ይሆናሉ ብሎ ማለም ደግሞ እነ አቶ መለሰ ዜናዊ ከሥልጣን ኮርቻቸው በገዛ ፈቃዳቸው ለመወረድ ዝግጁ ይሆናሉ እንደማለት ያህል የአሕዴግ መሪዎች የያዙትን ፀረ-ሕዝብ የዓላማ ፅናትና ቁርጠኝነት ከቁጥር የማያስገባ አደገኛ አስተሳሰብ ነው፡፡ በመሆኑም በአገራችን ትርጉም ያለው ብሔራዊ እርቅና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር እውን እንዲሆን በቅድሚያ እነዚህ የጥፋት ኃይሎች ከያዙት አክራሪ፥ ፀረ ዴሞክራሲያዊና ሽብርተኛ አካሄድ ሚሊዮኖችን በሚያሳትፍ ሕዝባዊ ትግል እንዲያፈገፍጉ መገደድ ይኖርባቸዋል፡፡

ሦስተኛ ከዚህ ከፊታችን አፍጥጦና አግጥጦ ከተደቀነው ሐቅ እንነሳ ካልን የሕዝባችን በሚሊዮን እየተቆጠረ መልሶ ከትግሉ የመደባለቁ ጉዳይ በዴሞክራቶችና በአገር-ወዳዶች ጎራ እንደ ዋና አጀንዳ መያዝና ጥረታችን ሁሉ ለዚህ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ ጉዳይ የኢሕአዴግ መሪዎች አካሄድና አቋም ከፀሐይ ደርቶ የሚታይ ነው፡፡ የነሱ ዋና የትግል አጀንዳ በቅድመ ግንቦቱም ወቅት ሆነ ኪዚያ በተከተሉት ወራት እንደታየው ሕዝባችን በሚሊዮን እየተቆጠረ ተመልሶ ትግሉ ውስጥ እንዳይደባለቅባቸው ነው፡፡ በመሆኑም ሕዝባችንን ይዘን በሰላማዊ ሰልፍም፥ በሥራ ማቆም አድማም ሆነ በሌሎች ሠላማዊና ሕጋዊ የትግል ስልቶች እየተጠቀምን ወደ ፊት እንዳንራመድ ዛሬ በአገራችን ሕዝብን ይዞ ታግሎ ማታገል በሕገ-ወጥነት የተፈረጀ ወንጀል ሆኗል፡፡ ሽብርተኞቹ ገዥዎች በዚህ በኩል ያላቸውን ቁርጠኝነት የቅንጅትን መሪዎች " እጅ ተወርች " አስረው ሲፈቷቸው በግልፅ ያሳዩ ይመልለናል፡፡ የሕዝባችን ተሳትፎ በዚህ መልክ ሕገ-ወጥ በሆነ ተአቅቦ በተገደበበት ሁኔታ ይኸን አሻፈረኝ ብሎ ትግሉን ለማፋፋም ቢሞከር እነዚህ የጥፋት ኃይሎች በሕዝባችን ላይ በለየለት አመፅ እንሚሰማሩበት ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡

አራተኛ ከዚህ እውነታ በመነሳት ዛሬ በአገራችን ሕዝብን ይዞ መታገል አስቸጋሪ ነው የሚሉ ወገኖች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለነዚህ ወገኖቻችን ያለን መልስ " አዎን አስቸጋሪ ነው፥ የኢትዮጵያችን የነፃነት ተጋድሎ የአልጋ ባልጋ ጉዞ ሆኖም አያውቅ፥ አይደለም፥ ወደ ፊትም አይሆንም" የሚል ነው፡፡ እንዲያውም የትግል ስትራቴጂያችንን ለመንደፍ ስንነሳ መንደረደሪያ አድርገን የምንወስደው ይኸን መራራ ሐቅ አስቀድመን በመቀበል ከዚህ የሚፈልቁትን የዓላማ ፅናት፥ የትግል አንድነት፥ ወዘተ... የመሳሰሉትን እሴቶች በማንገብ ነው እንላቸዋለን፡፡ ከዚያ አልፈው በዚህ ሁኔታ እንዲህ ዓይነቱ ሕዝባዊ ትግል "አይቻልም" ለማለት የሚቃጣቸው ኃይሎች እንዳሉም የዚያኑ ያኽል ግልፅ ነው፡፡ ለነዚህ ደግሞ ያለን አጭር መልስ የአገር ኅልውና፥ የአገርና የሕዝብ ሰላም፥ የአገር አንድነትና ብልፅግና፥ የሕዝብ መብት ጉዳይ ስለሆነ " መቻል አለበት" የሚልና ላለው ሽብርተኛ  አገዛዝ የሚመጥን የጋራ ትግል ስትራቴጂ መንደፍ ያስፈልገናል የሚል ብቻ ይሆናል፡፡ "መቻል አለበት" ብለን ከተነሳን ደግሞ በአድር-ባይነትም ሆነ በትግሉ ከባድነት ተሸንፈው ሕዝባችንን ይዞ መታገል አይቻልም የሚለውን ተንበርካኪ እምነታቸውን ለመሸፋፈን ሲሉ ብቻ ይኽ ዓይነቱ ትግል "አያስፈልግም" ሌላ "የተሻለ፥ የሰለጠነና የሰከነ የድርድር፥ የሽምግልና፥ የዓለም አቀፍ ጫና" የሚባል አካሄድ አለን የሚሉ ኃይሎች ለትግላችን ጥራት፥ አንድነትና ጥንካሬ ስንል ልንታገላቸው ይገባናል፡፡

እንዲያውም በቅንጅቱም ሆነ በሌሎች በተቃዋሚው ጎራ በተሰለፍነው ኃይሎች ውስጥና መኻል የፖለቲካ ልዩነቶች አሉ ከተባለ ሌላ ሌላውን ሁሉ ትተን እነዚህ ልዩነቶች ከዚህ የአገራችን ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች ፅኑ ዓላማና የጋራ ስትራቴጂ አንፃር እየተፈተሹ ማን ከሕዝብ ወገን ቆሞ ሕዝብን ይዥ ልታገል እንደሚል፥ ማን ደግሞ ሕዝባዊውን ትግል የሚያዘናጋ አካሄድ እንደያዘ ግልጥልጥ ብሎ የሚወጣበት በቁም ነገር ላይ ያተኮረ ክርክር እንዲካሄድ፥ ይኸን አሻፈረኝ ብሎ ደግሞ ከክርክር ለመሸሽ የሚሞክር ወገን ካለ ደግሞ በሕዝብ ፊት በትግል እንቅፋትነቱ እንዲጋለጥ መጣር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ክርክር የግድ የሚሆንበት ምክንያት ለኛ በጣም ግልፅ ነው። ዛሬ በአለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ "ጥቃቅን" ሊባሉና በማነታረክ ላይ ካሉት ልዩነቶች በስተጀርባ ላለፉት ሁለት ዓመታት ከታማኝ "ተቃዋሚዎች" ጎራ ሲንፀረባረቅ የቆየው ትግል አዘናጊ አቋም "በሰለጠነ ፖለቲካ" ሰበብ መልሶ በሌሎች ሊቀርብልን ዳር ዳር እየተባለ እያየን ነው። ይኸ "የትግል" ስትራቴጂ የኢሕአዴግ መሪዎች በሸብር የጨበጡትን ሥልጣን በድርድር፥ በብሔራዊ እርቅ መንፈስ፥ በአገር ሽማግሌዎች ጥረትና በዓለም-አቀፉ ጫና አስለቅቀን የአገራችንን ችግሮች የሕዝባዊ ትግል "ጫጫታና ግርግር" ሳያስፈልገን በሰከነና "በሰለጠነ" ፖለቲካ እንፈታለን የሚል ከፍ ብለን እንደጠቆምነው የፀረ-ሕዝቦቹን የዓላማ ግልጽነትና ቁርጠኛነት ከቁጥር የማያስገባ እጅግ አደገኛ ትግል አዘናጊና አነሁላይ አካሄድ ነው። አሁን ዳር ዳር እንደሚባለው ከሆነ የዚህ ሴረኛ አካሄድ ሁለት ምእራፎች ወይም "መቋጠሪያዎች" እየተቃዱለት እንደሆነ የሚጠቁሙ አንዳንድ ክስተቶች እየታዩ ነው።

በአንድ በኩል በሕዝባዊነታቸው ፀንተው የቆሙትን ኃይሎች በ"አክራሪነት" ፈርጆ በሚያገልል ሁኔታ አንዳንድ ተቃዋሚ ተብየዎች፥ የኢሕአዴግ ተወካዮችን፥ የአገር "ሽማግሌዎችንና" አንዳንድ ባዕዳንን ባካተቱ ድርድር ተብየ መመሳጠሮች አማካይነት የአገራችንን ችግሮች "ለመፍታት" ሙከራዎች እየተደረጉ ናቸው። በመሞከር ላይ ያለው አጥፊ ሂደት በነዚህ ማንም ባልወከላቸው ኃይሎች መኻከል ስለ ቀጣዩ ምርጫ የሆነ "ስምምነት" ላይ እንዲደረስና በዚህ መልክ የግንቦት ታሪካዊ የትግል ምእራፍ ሥርዓተ-ቀብር ተካሂዶ "ዴሞክራሲ በሂደት" በሚል ሰበብ ሕዝባችን ከምርጫ ምርጫ እየተንከራተተ ባልሆነ አቀጣጫ እንዲኳትን የሚጋብዝና ለአገዛዙ ዕድሜ-ቀጣይ ከመሆን ሌላ ለአገራችን ችግሮች ምንም መፍትኄ የማያመጣ አደገኛ ሴራ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ኅብረተሰቡን አግልሎ በፀረ-ሕዝብ ክፍሎችና ማንንም በማይወክሉ "ተቃዋሚዎች" መኻከል በፈረንጆቹ አማካይነት በሚደረግ መደራደር/ መመሳጠር የአገራችን ችግሮች ይፈታሉ ማለት የስመ-ጥፉውን የለንደን ጉባዔ (ኮንፈረንስ) አደገኛ አካሄድ መድገም ስለሚሆን ሕዝባችንን ይዘን በአንድ የተባበረና የጋራ ድምፅ "አድርሰናል" ማለት ይኖርብናል። እንዲህ ዓይነቱ "አሻፈረን" ባይነት ግን ብቻውን ለንደን ላይ የትም እንዳላደረሰን ሁሉ ዛሬም የትም አያደርሰንም።
አግላዩ የለንደን ጉባዔ ለምን በተካሄደበት መልክ ተካሂዶ ለአገራችን የጥፋት ምእራፍ ለመክፈት ቻለ? በዚያም የታሪክ ወቅት የአገር አንድነት፥ የሰላም፥ የዴሞክራሲና የብሔራዊ ክብር አጀንዳ ልክ እንደ ዛሬው ሚሊዮኖች ከዳር እስከ ዳር ያነገቡት አጀንዳና ህልም ነበር። ሆኖም በዚያ ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያችን እጣ ፈንታ በጥቂቶች ሲወሰን ይኸ የሕዝብ ራእይና አጀንዳ - ከተበታተኑ ሚሊዮኖች በስተቀር - ተኣማኒነት ያለው ሰብሳቢ ኃይል ስላልነበረው ሰላሟና ዴሞክራሲዋ ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ አንድነቷንና ኅልውናዋን እንኳን የቅድሚያ ቅድሚያቸው ሳይሆን ጉዳያቸው ባልሆነ ኃይሎች ብቻ እንዲወሰን ሆነ።
ዛሬም ቢሆን እነዚህ ብዙዎች መስዋዕት የሆኑባቸውና የሚሆኑባቸው እሴቶች የሚሊዮኖች ናቸውና ... እያልን የምንዘናጋበት ምንም ምክንያት የለም። የሚሊዮኖች ህልም እንደ ለንደኑ በጥቂቶች ሴራ ለጊዜውም ቢሆን ሊጠለፍ ይችላል። ደጋግመን ለመጠቆም እንደሞከርነው ዛሬም እንደ ትላንቱ በግንቦት ዘጠና-ሰባት ሳቢያ ሕዝባችን የራሱ ዕድል ወሳኝና ለመብቱ ለመቆም ያልውን ጥማት ብቻ ሳይሆን ብቁነቱን ያሳየባችውን የአንድነት፥ የሰላም፥ የዴሞክራሲና የፍትኅ እሴቶች ሰብሳቢ ሁነኛ ኃይል እንዲያጡና "የሽግግር ክፍተት" እንዲፈጠር እየተሞከረ ነው። ቀደም ሲል እንደጠቀስነው አገራችን ዓለም-አቀፍ ይዘት ባለው አዲስ የፍትጊያ ውጥንቅጥ አጣብቂኝ ውስጥ መሆኗ በተገቢ ሊጤን ይገባል። የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች በጋራ መቆማቸውን ትተው በምንም ምክንያት ይሁን በምን እንዲህ ዓይነቱ መዘዘኛ ሴራ እንዲቀጥልና እንዲሳካ ከፈቀዱና እንደ ለንደኑ ወቅት ምናልባትም በባሰ መልኩ ይቺ አገራችን ሁነኛ ባለቤት ያጣች የትርምስ ቤት ከሆነች የየካቲት ቅልበሳ የጀመረውን ፈተና ግንቦት ሊጨርሰው የሚችልበት ሁኔታ አለ። በዚህ ደግሞ ሁላችንም ተጠያቂነት ይኖርብናል። ይኸንን ከፍተኛ አደጋ ለመከላከል እርባና ባላቸው የሕዝባችን እሴቶች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች በፀረ-ሕዝቦቹ ከመቀደማቸው በፊት የኢትዮጵያችን እጣ ፈንታ ሲወሰን ማንም ሊያልፈው የማይችል በሕዝባችንም ፊት ሆነ በማንም ይሁን በማን ዓይን ተኣማኒነት ያለው ሰፊ መሠረት ያለውና አገራዊና ሕዝባዊ መርኅ ላይ የቆመ ሃቀኛ የጋራ መድረክ የማቋቋሙ ጉዳይ እጅግ አጣዳፊ ተግባርና አገራዊ ግዴታ ነው እንላለን።

ዛሬ በቅንጅት የተለያዩ ክፍሎችም ሆነ በጠቅላላው የተቃዋሚ ጎራ ልዩነት፥ ክርክር፥ ወዘተ... አለ ከተባለ በነዚህ ቁም-ነገሮች ላይና በጠራ መስመር በጋራ ስለመታገል ጉዳይ ሁሉም ያለውን አቋም በግልፅ አንግቦ እንዲከራከር መጋበዝም አሻፈረኝ ካለ ደግሞ መገደድም ይኖበታል። እንዲህ ዓይነቱ ሕዝብንና አገርን ማዕከል ያደረገ የሰከነ ውይይት፥ ምክክርና ክርክር ለቀጣዩ ትግል ወሳኝ የሚሆነውን ያኽል በአንዳንድ ወግኖቻችን በኩል ከዚህ ዓይነቱ ጤናማ ሂደት የመሸሽ ሁኔታ እንዳለ ላለፉት ሁለት ዓመታት ስንታዘብ ቆይተናል። በአዳራሽ ስብሰባዎችም ሆነ በተለያዩ የውይይት መድረኮች የሕዝብ ጉዳይ ነውና በሕዝብ ፊት

እንከራከር ስንል፥ ወሳኝ ወደሆነው ወደ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ እውንነት እንሥራ እያልን ስናሳስብ፥ ሕዝብ “ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ” ቢልም ዛሬ ድምፅ ለሌለው ሕዝባችን ድምፅ ሆነን በጋራ ሆነን እሮሮውን እናሰማ እያልን ስንወተውት ጆሮ ዳባ ሲባል ቆይቷል። ለትግላችን ጥራት ሲባል ይኽ ቧልት ከእንግዲህ መቆም አለበት እንላለን።
ልዩነቶችን አጣቦና ተቻችሎ ከግልና ከድርጅት በእጅጉ በላቁ አገራዊና ሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ መተባበር አስፈላጊነቱን ሁሉም ቢለውም ዋናው ቁም-ነገር ይኽንን በተግባር የመተርጎሙ ጉዳይ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቅንጅት ወገኖቻችን ውስጥ የተከሰተው ችግር እንዲፈታ ጥረት በማድረግ ፋንታ አሁን እንደምንታዘበው ከሆነ በተለይ በአንዳንድ ስድ የሆኑና አክራሪ ወገንተኝነትንና ቡድንኝነትን በያዙ ድረ-ገፆች የሚስተጋባው ሁካታ አሳዛኝ ሆኖ አግኝተነዋል። እነኝህና ሌሎች የመናኛ መድረኮች የአገርንና የሕዝብን ጥቅም ያስጠበቀና የሰከነ ውይይት የሚደረግባቸው ሳይሆን እሰጥ-አገባ የንትርክ መድረኮች በመሆን አሉ የተባሉ እዚህ ግቡ የማይባሉ ልዩነቶች የበለጠ የሚራገቡበትና ከፖለቲካ ግንኙነት ዘሎ ሰብዓዊና ዜጋዊ ትስስርን የሚበጣጥሱ ፍጹም ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የጎደላቸው ሆነው በማግኘታችን አዝነናል። ለእኛ ግልጽ ያልሆኑ ሌሎች ከበድ ያሉ ምክንያቶች ከሌሉ፥ እስከ አሁን ልዩነቶች ተብለው ሲቀርቡ በትዝብት የምንሰማቸው ጥቃቅን የአሠራር፥ የተክለ-ሰብ፥ የገንዘብ፥ የሥልጣን፥ ወዘተ… ከሆኑ በተያዘው መልክና ሁኔታ የሕዝባችንን የትግል ቅስም ሊሰብር በሚችል ንትርክ ሳይሆን “ገበና ሳያሳዩ” በውስጥ በሚደረግ የሰከነ ውይይት እንዲፈቱ፥ ሆኖም አሉ የሚባሉት ልዩነቶች የፖለቲካ ይዘት ያላቸው ከሆነ ደግሞ በሕዝብ ፊት በግልፅ ይፋ ወጥተው መልክ ያለው ውይይት እንዲደረግባቸው አገራዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። እስከ አሁንም ኢዴኃኅ (ኅብረቱ) ይዞት የቆየው በማንኛውም የሌላ ድርጅት የውስጥ ጉዳይ በምንም መልክ ጣልቃ ያለመግባት ቋሚ ውሳኔና በዚሁ መንፈስ በቅንጅቱ መኻል በተከሰተው አሳዛኝ ልዩነት ወገን ለይተን ላለመገኘት የወሰድነው መርኃዊ አቋም የቅንጅቱን የውስጥ ጉዳይ ለቅንጅቱ መተው አግባብ ያለው ሆኖ ስላገኘነው ነው። ይኽ ጥሪያችን ለነዚህ ወገኖቻችን ብቻ ሰይሆን በጠቅላላው ለአገራችን ዴሞክራትና አገር-ወዳድ ኃይሎችም ነው። ከትግላችን ዓላማዎች አንዱ በኅብረሰተባችን ዴሞክራሲና ተጠያቂነት እንዲሰፍኑ ለማድረግ ነው። ነገር ግን ተጠያቂነትን ከኢሕዴግ መሪዎች ብቻ አንጠይቅም። አንድ ትግል የተዋጣ የሚሆነው ጥሩ መሪዎች ብቻ ሳይሆን ጥሩ ተመሪዎች ሲኖሩት ነው። ጥሩ ተመሪ ደግሞ የቆመው ለዓላማ፥ ለአገር፥ ለወገን አንጂ ለድርጅትና ለግለሰብ ስላይደለ ከመሪዎቹም ተጠያቂነትን መጠየቅ አለበት እንላለን። ይኽንን ድርጅት በጭፍን፥ ይኽን ግለብ በሙሉ እምነት፥ ያንን ቡድን ዓይን ጨፍነን እንደግፋለን በሚል ወገንተኛነት ሳይሆን ጎራ ከመለየት በፊት ሁሉም ረጋ ብሎ ልዩነቶች ሲከሰቱም ሆነ ድጋፍ ለመስጠትና ለመንፈግ በምን አቋም? በምን መስመር? በምን ስትራቴጂ? በምን የፖለቲካ መስመር ብሎ ራስን መጠየቅ ያስፈልጋል።

ዛሬ ካለንበት አደገኛ ውኸንብር ወጥተን ለአገራችንና ለቀጣይ እንግልት ለተዳረገ ሕዝባችን አንድ ቁም-ነገር እንሥራ የሚል ዜጋ ሁሉ በያለበት በትርኪ ምርኪውና በአልባሌ ነጥቦች ላይ መራኮቱን ትቶ በነዚህ ቁም-ነገሮች ላይ ብቻ የሰከነ ውይይት፥ ምክክርና ክርክር እንዲካሄድ መጠየቅ የዜግነት መብቱና የታጋይነት ግዴታው ነው። አንዳንዶች ትግላችንንና አገራችንን በጥፋት ጎዳና ይዘው ለመንጎድ ቢሞክሩ ታጋዩ ሕዝብ ይኽንን አሻፈረን ብሎ፥ ተስፋ አስቆርጦ በአገር ጉዳይ በቁም-ነገር የሰከነ ውይይት እንዲካሄድ ሁሉም የተቻለውን አስተዋጽዖ ማድረግ ይጠበቅበታል። ኅብረታችን የትም ቢሆን፥ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ለእንዲህ ዓይነቱ ጤናማ ውይይትና ከዚህ ብቻ ሊፈልቅ ለሚችለው ሕዝብንና አገርን ላስቀደመ ሃቀኛ የጋራ የትግል መድረክ የሚጠበቅበትን አገራዊ ግዴታ ለመወጣት እንደ ምንጊዜውም ዛሬም ዝግጁ መሆኑን ይገልጻል። ለሚያልፍ ጊዜኣዊ ፍላጎትና እንደ ጤዛ ለሚረግፍ ዝና ወይም ቡድናዊ ስሜት ሳንሸነፍ፥ ከግልና ከቡድን ወይም ከድርጅት በላይ ለሆነ ሕዝባዊና አገራዊ ዓላማ እራሳችን ተገዥ ማድረግ ነገ ለምንመኘውና ለምንታገልለት የፍትኅ፥ የእኩልነትና የአንድነት እውን መሆን ቁልፍ መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል እንላለን። የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ቁንጮዎች የገደዳቸው መቻቻል በእኛም ሊንጸባረቅ አይገባውም።

ኢዴኃኅ በኢትዮጵያ ሕዝብ አርቆ አስተዋይነትና ታጋሽነት ይመካልና አሁንም በተቃዋሚው ጎራ በተፈጠሩ አንዳንድ ጊዜኣዊ አለመግባባቶች በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ያለው ወገናችን ተስፋ ሳይቆርጥ በተለመደው ትዕግስቱ ለመብቶቹ መከበርና ለአንድነቱ ከሚደረገው ትግል ላፍታም እንዳይዘናጋ አደራችን የጠበቀ ነው።

የጋራ ችግሮቻችንን በጋራ እንወጣ!
የተባበረ ትግል ለአስተማማኝ ድል!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!
የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)